ቅዳሴ፡ እግዚእ።

፩፤ እመጽሐፈ፡ ኪዳን፡ ዘነገሮሙ፡ እግዚእነ፡ ወመድኃኒነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እምቅድመ፡ ዕርገቱ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ እምድኅረ፡ ትንሣኤሁ፡ እሙታን ።በረከተ፡ ጸጋሁ፡ ወሀብተ፡ ረድኤቱ፡ የሀሉ፡ ምስለ፡ ....

.... ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን ።

፪፤ ይ፡ ዲ፡ በሰማይ፡ የሀሉ፡ ልብክሙ ።

ይ፡ ሕ፡ እወ፡ በሰማይ፡ የሀሉ፡ ልብነ፡ በእንተ ስምከ፡ አጽንዐነ፡ ወረስየነ፡ ድልዋነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እግዚእነ፡ ወአምላክነ ።

፫፤ ይ፡ ዲ፡ ወለእመቦ፡ ዘተሐየሰ፡ ምስለ ቢጹ፡ ይኅድግ፡ ሎቱ ።

ይ፡ ሕ፡ ለለምዕራፉ፡ በከመ፡ ምሕረትከ፡ አምላክነ፡ ወእከ፡ በከመ፡ አበሳነ፡ ፫ተ፡ ጊዜ፡

፬፤ ይ፡ ዲ፡ እመቦ፡ ዘሐለየ፡ በልቡ፡ ኑፋቄ፡ ይትጋነይ ።

ይ፡ ሕ፡ በከመ፡ ምሕረትከ፡ አምላክነ፡ ወእከ፡ በከመ፡ አበሳነ ።

፭፤ ይ፡ ዲ፡ እመቦ፡ ነውረ፡ ሐሊና፡ ዘቦ፡ ኢይቅረብ ።

ይ፡ ሕ፡ በከመ፡ ምሕረትከ፡ አምላክነ፡ወእከ

የጌታ፡ ቅዳሴ ።

፩፤ ጌታችንና፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከሙታን፡ ተለይቶ፡ ከተነሣ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ከማረጉ፡ በፊት፡ ለሐዋርያት፡ ከነገራቸው፡ ከመጽሐፈ፡ ኪዳን፡ የጸጋው፡ በረከት፡ የረድኤቱም፡ ሀብት፡ በጳጳሳችን፡ .... በእገሌ፡ .... ላይ፡ ይኑር፡

፪፤ ይ፡ ዲ፡ ልቡናችሁ፡ በሰማይ፡ ይኑር።

ይ፡ ሕ፡ አዎን፡ ልቡናችን፡ በሰማይ፡ ይኑር። ስለ፡ ስምህ፡ አጽናን፡ ጌታችንና፡ አምላካችን ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሆይ፤ የተዘጋጀንም፡ አድርገን ።

፫፤ ይ፡ ዲ፤ ከወንድሙ፡ ጋራ፡ የተጣላ፡ ቢኖር፡ ይተውለት ።

ይ፡ ሕ፡ በየምዕራፉ፡ አምላካችን፡ሆይ፡ እንደ ቸርነትህ፡ ነው፡ እንጂ፡ እንደ፡ በደላችን፡ አይሁን፡ ፫ት፡ ጊዜ።

፬፤ ይ፡ ዲ፡ በልቡ፡ መጠራጠርን፡ ያሰበ፡ ቢኖር፡ ይመን ።

ይ፡ ሕ፡ አምላካችን፡ ሆይ፡ እንደ፡ ቸርነትህ ነው፡ እንጂ፡ እንደ፡ በደላችን፡ አይሁን ።

፭፤ ይ፡ ዲ፡ የአሳብ፡ ነውር፡ ያለበት፡ ቢኖር፡ አይቅረብ ።

ይ፡ ሕ፡ አምላካችን፡ ሆይ፡ እንደ፡ ቸርነትህ

በከመ ፡ አበሳነ ።
፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እመበ ፡ ዘወድቀ ፡ በኃጢአት ፡
ኢይርሳዕ ፡ እስመ ፡ ዘኢይትረሳዕ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ
በከመ ፡ አበሳነ ።
፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እመበ ፡ ድውየ ፡ ሕሊና ፡ ዘቢ ፡
ኢይቅረብ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ
በከመ ፡ አበሳነ ።
፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እመበ ፡ ስዑብ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ን
ጹሐ ፡ ይትገኃሥ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ
በከመ ፡ አበሳነ ።
፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እመበ ፡ ነኪር ፡ እምትእዛዙ ፡
ለኢየሱስ ፡ ይትከላዕ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ምሕረትከ ፡ አምላክነ ፡ ወአኮ
በከመ ፡ አበሳነ ።

፲ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እመበ ፡ ዘያስተሐቅር ፡ ነቢያ
ተ ፡ ያግኅሥ ፡ ርእሶ ፡ እመዓተ ፡ ዋሕድ ፡ ወ
ያድኅን ፡ ነፍሶ ።
፲፩ ፡ መስቀለ ፡ ኢይግፉዕ ፡ ወይጕየይ ፡ እመ
ዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ዘይሬእየነ ፡ ብነ
አብ ፡ ብርሃን ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ ወመላእክቲሁ
ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ይሔውጹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፪ ፡ ነጽሩ ፡ ነፍሰክሙ ፡ ወአንጽሑ ፡ ነፍ
ስተክሙ ፡ ወለቢጽክሙሂ ፡ ኢትዝክሩ ፡ አበ
ሳሁ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ መኑሂ ፡ ኢየሀሉ ፡ በመ
ዓት ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ።
፲፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሬኢ ፡ አልዕሉ ፡ አል
ባቢክሙ ፡ ንቅረብ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ሕይወት ፡
ወቅድሳት ፡ በጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንንሣእ
ዘተውህበ ፡ ለነ ፡ ጸጋ ።

፲፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።
ይ ፡ ካ ፡ አእኵትዎ ፡ ለአምላክነ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ርቱዕ ፡ ይደሉ ።
ይ ፡ ካ ፡ አልዕሉ ፡ አልባቢክሙ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ብነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር አምላክነ ።

ነው ፡ እንጂ ፡ እንደበደላችን ፡ አይሁን ።
፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በኃጢአት ፡ የወደቀ ፡ ቢኖር ፡
አይርሳ ፡ የማይረሳ ፡ ነውና ።
ይ ፡ ሕ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ
ነው ፡ እንጂ ፡ እንደበደላችን ፡ አይሁን ።
፯ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ አሳቡ ፡ ድውይ ፡ የሆነ ፡ ቢኖር
አይቅረብ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደቸርነትህ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይሁን ።
፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚሠራ ፡ ንጹሕም
ያልሆነ ፡ ቢኖር ፡ ይወገድ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ በደላችን ፡ አይሁን ።
፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ከኢየሱስ ፡ ትእዛዝ ፡ ልዩ ፡ የሆነ
ቢኖር ፡ ይከልከል ።
ይ ፡ ሕ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንደቸርነትህ
ነው ፡ እንጂ ፡ እንደበደላችን ፡ አይሁን ።

፲ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ነቢያትን ፡ የሚያቃልል ፡ ቢኖ
ር ፡ ከዋሕድ ፡ (ከወልድ ፡) መዓት ፡ ራሱን ፡ ያርቅ
ነፍሱንም ፡ ያድን ።
፲፩ ፡ መስቀልን ፡ አይበድል ። ከእግዚአ
ብሔርም መዓት ፡ ይራቅ ፡ የሚያየን ፡ ብርሃን ፡
አብ ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከሚ
ጐበኙ ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክትም ፡ ጋራ ፡ አለና ።

፲፪ ፡ ነፍሳችሁን ፡ ተመልከቱ ፡ ሰውነታች
ሁንም ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ፡ የባልንጀራችሁንም
በደል ፡ አታስቡ ፡ ማንም ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር
በቍጣ ፡ እንዳይኖር ፡ አስተውሉ ።
፲፫ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያያል ፡ ልቡናችሁን
ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጉ ። ወደ ፡ ሕይወት ፡ መድ
ኃኒት ፡ እንቅረብ ፡ ጸጋ ፡ ሁኖ ፡ የተሰጠነንም
ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ በእግዚአብሔር ጥበብ
እንቀበል ።
፲፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሁላችሁ ፡
ጋራ ፡ ይሁን ።
ይ ፡ ሕ ፡ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።
ይ ፡ ካ ፡ አምላካችንን ፡ አመስግኑት ።
ይ ፡ ሕ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይገባል ።
ይ ፡ ካ ፡ ልቡናችሁን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጉ ።
ይ ፡ ሕ ፡ በአምላካችን ፡ እግዚአብሔር ዘንድ
አለን ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቅዱስ ፡ በቅዱሳን ፡ ፫ት ፡ ጊዜ

ይ ፡ ሕ ፡ ወትረ ፡ በሰማይ፡ወበምድር፡፫ት ፡ ጊዜ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ካ ። ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግ
ዚ አ ብ ሔ ር ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግ
ዚ አ ብ ሔ ር፡ አምላክ ፡ አማልክት ፡ ዘሀሎ፡ወይ
ሄሉ ፡ ወትረ ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ።

፲፯ ፤ አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ዘእግዚእነ ፡ ወአ
ምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢ የሱ ስ ፡ ክ ር ስ ቶ ስ ።
በረከተ ፡ ማህሉ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ

....
.... ለዓለመ፡ዓለም ፡ አሜን ።
....

፲፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንአኵተከ ፡ አምላክ ፡ ቀዱስ ፡
ፈጻሜ ፡ ነፍስነ ፡ ወሀቤ ፡ ሕይወትነ፡ ዘኢይማ
ስን ፡ መዝገብ፡ አቡሁ ፡ ለዋሕድ ፡ ወልድከ ፡
መድኃኒነ ፡ ዘይዜኑ ፡ ዘዚአከ ፡ ፈቃደ ፡እስመ ፡
ፈቀድከ ፡ ከመ ፡ ንድኃን ፡ ብከ ።

፲፱ ፤ የአኰተከ ፡ ልብነ ፡ እግዚኦ ፡ አንተ ፡
ኀይሉ ፡ ለአብ ፡ ወጸጋ ፡ ለአሕዛብ ። አእምሮ
ርትዕ ፤ ጥበበ ፡ ስሑታን ፡ መፈውሰ ፡ነፍስ ፡
ዕበየ ፡ ትሑታን ፤ ሀገሪትነ ።

፳ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ምርጕዘ ፡ ጻድቃን
ተስፋሆሙ ፡ ለስዱዳን ፤ መርሶሆሙ ፡ ለአለ
ይትሀወኩ ። ብርሃነ ፡ ፍጹማን ፤ ወልደ ፡ አም
ላክ ፡ ሕያው ፤ አብርህ ፡ ላዕሌነ ፡ እምዘኢይት
አተት ፡ ጸጋከ ፤ ትክለተ ፡ ወጽንዐተ ፡ ተአም
ኖ ፡ ወጥበበ ፡ ወኃይለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘኢይፀ
ንን ፡ ወዘኢይትመየጥ ፡ ተስፋ ።

፳፩ ፤ አእምሮ ፡ መንፈስ ፡ ሀብ ፡ ለትሕትናነ፡
ከመ ፡ ዘልፈ ፡ በርቱዕ ፡ ንጹሓነ ፡ ንኩን፡ አግ
ብርቲከ ፡ እግዚኦ ። ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኪያከ
ይሴብሑ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ኪያከ ፡ እግዚኦ፡ ንአኵት፡ ወንሴብሐከ

፳፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ ።

፲፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በቅዱሳን ፡ ዘንድ ፡ የተመሰገነ፡
፫ት ፡ ጊዜ ፡

ይ ፡ ሕ ፡ ዘወትር፡በሰማይና፡በምድር፤፫ት ፡ ጊዜ።

፲፮ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚ
አብሔር ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡
እግዚአብሔር ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፤ ዘወት
ር ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለ ፡ የሚኖርም ።

፲፯ ፤ የጌታችን ፡ የአምላካችንና ፡ የመድ
ኃኒታችን ፡ የ ኢ የ ሱ ስ ፡ ክ ር ስ ቶ ስ ፡ የቍርባን ፡
ምስጋና ። የይቅርታው ፡ በረከት፡

....
.... ላይ ፡ ይኑር ፤ ለዘላለሙ ፡
አሜን ።

፲፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ቅዱስ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ እና
መሰግንሃለን ፤ ነፍሳችንን ፡ ፍጽምት ፡ የምታ
ደርግ ፡ ሕይወታችንን፡ የምትሰጥ ፤ የማይጠፋ
መዝገብ ፡ ያንድ ፡ ልጅህ ፡ የመድኃኒታችን ፡
አባት ፤ ያንተን ፡ ፈቃድ ፡ የሚናገር ። ባንተ ፡
እንድን ፡ ዘንድ ፡ ወደሃልና ።

፲፱ ፤ አቤቱ ፡ ልባችን ፡ ያመሰግንሃል ፡ የአብ
ኃይሉ ፡ የአሕዛብም ፡ ጸጋ ፡ አንተ፡ ነህ ። የቅን
እውቀት ፤ የስሑታን ፡ ጥበብ ፤ ነፍስን ፡ የምታ
ድን ፤ ለተዋረዱት ፡ ክብር ፡ አገራችን ።

፳ ፤ የጻድቃን ፡ ምርኩዝ ፡ ለተሰደዱት ፡ ተስ
ፋቸው ፤ ለሚታወኩት ፡ ጸጥታቸው ፡ አንተ
ነህ ። የፍጹማን ፡ ብርሃን ፡ የሕያው ፡ አምላክ
ልጅ ፡ ከማይለይ ፡ ጸጋህ ፡ አብራልን ፤ መተክ
ልን ፡ መጽናትንም ፡ መታመንና ፡ ጥበብን ፡
የማይዘነብል ፡ የሃይማኖትን ፡ ኃይል ፡ የማይ
ለወጥ ፡ ተስፋንም ።

፳፩ ፤ የነፍስ ፡ ዕውቀትን ፤ ለትሕትናችን ፡
ስጥ ፤ አቤቱ ፡ እኛ ፡ ባሮችህ ፡ በሚገባ ፡ ዘወ
ትር ፡ ንጹሓን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ።
ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ አንተን ፡ ያመሰግናሉ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ አንተን ፡ እናመሰግናለን ፡
እናከብርሀማለን ።

፳፪ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ በእንተ ፡ ብፁዕ፡ ቅዳ ፡ ሐዋ ፡
ቍ ፡ ፳-፱ ፡ እይ ።

፳፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ።

፳፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መሐርሙ ፡ እግዚኦ ወተሣሀሎሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

፳፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ እወ ፡ እግዚኦ ፡ ኪያከ ፡ ነአኵት ፡ ወኪያከ ፡ ንበርከ ፡ ወዘልፈ ፡ ንስእለከ እግዚኦ ፡ አበ ፡ ልዑላን ፡ ዘይነግሥ ፡ ለመዘግብተ ፡ ብርሃን ።

፳፮ ፤ ሐወጻ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ እምሰማያት እግዚአሙ ፡ ለሥልጣናት ፡ አርእስተ ፡ መላእክት ፡ ወኃይለ ፡ አጋዕዝት ፡ ወስብሐተ ፡ መናብርት ፤ ዐፀፍተ ፡ ብርሃናት ፡ ትፍሥሕተ ፡ ፍግዕ ፡ ወንጉሠ ፡ ነገሥት ፤ አብ ፡ ዘይእኅዝ ፡ ኵሎ ፡ በእድ ፡ ወይመልክ ።

፳፯ ፤ ወበምክረ ፡ ዚአከ ፡ ወልድከ ፡ ዋሕድ ፡ ዘተሰቅለ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒትነ ።

፳፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ተንሥኡ ።
ይ ፡ ካ ፡ ዘበቃለ ፡ ኪዳንከ ፡ በቱ ፡ ኵሎ ፡ ገበርከ ፡ ሠሚረከ ፡ በቱ ።
፳፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ውስተ ፡ ጽባሕ ፡ ነጽሩ ።
ይ ፡ ካ ፡ ወፈነውከ ፡ ውስተ ፡ ማኅፀነ ፡ ድንግል ተፀንሰ ፡ በከርሥ ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፤ ወልደቱ ፡ ተዐውቀ ፡ እመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፴ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንነጽር ።
ይ ፡ ካ ፤ እምድንግል ፡ ተወሊዶ ፡ ከመ ፡ ፈቃደከ ፡ ይፈጽም ፡ ወሕዝበ ፡ ለከ ፡ ይሥራዕ ፡ ቅዱሰ ።

፴፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ አውሥኡ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ጸባዖት ፡ ፍጹም ፡ ምሉዕ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ ፡ ስብሐቲከ ።
፴፪ ፤ በዝየ ፡ ዕርገተ ፡ ዕጣን ፡ ወይዕጥን ፡ እደው ፡ ወያዕርግ ፡ በበፎቱ ፡ ሳዕስ ፡ ኅብስት ፡ ወጽዋዕ ።

ይ ፡ ካ ፡ ሰፍሐ ፡ እዴሁ ፡ ለሕማም ፡ ሐመ ፡ ከመ ሕሙማነ ፡ ያድኅን ፡ እለ ፡ ተወከሉ ፡ በላዕሌሁ ።

፳፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንፍቅ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ።
ቅዳ ፡ ሐዋ ፡ ፲-፳፩ ፡ እይ ።

፳፬ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ አቤቱ ፡ የጳጳሳቱን ፡ አለቆች ፡ ጳጳሳቱንና ፡ ኤጲስቆጶሳቱን ፡ ቀሳውስቱንና ፡ ዲያቆናቱን ፡ የክርስቲያንንም ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ማራቸው ፡ ይቅርም ፡ በላቸው ።

፳፭ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አቤቱ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አንተን ፡ እናመሰግናለን ፤ አንተን ፡ እናከብራለን ። የልዑላን ፡ አባት ፤ ለብርሃን ፡ መዝገቦች ፡ የምትነግሥ ፡ አቤቱ ፡ ዘወትር ፡ እንለምንሃለን ።

፳፮ ፤ በሰማያት ፡ ሆነህ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ጐብኘት ፤ የመላእክት ፡ አለቆች ፡ የሚሆኑ ፡ የሥልጣናት ፡ ጌታቸው ፤ የአጋእዝትም ፡ ኃይል ብርሃንን ፡ የተጐናጸፉ ፡ የመናብርትም ፡ ክብራቸው ፤ የደስታ ፡ ደስታ ፤ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ሁሉን ፡ በእጅ ፡ ይዞ ፡ የሚገዛ ፡ አብ ።

፳፯ ፤ አንድ ፡ ልጅህ ፡ ኢየሱስ ፡ በንተ ፡ ምክር ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ የተሰቀለ ።

፳፰ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ የተቀመጣችሁ ፡ ተነሡ ።
ይ ፡ ካ ፡ በቃልህ ፡ ኪዳን ፡ ወደህ ፡ ሁሉን ፡ በርሱ ፡ ያደረግህ ።
፳፱ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተመልከቱ
ይ ፡ ካ ፡ ወደ ፡ ድንግል ፡ ማኅፀንም ፡ ሰደድከው ። በማኅፀን ፡ ተፀነሰ ፤ ሥጋም ፡ ሆነ ፤ መወለዱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታወቀ ።
፴ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ እናስተውል
ይ ፡ ካ ፡ ከድንግል ፡ ተወልዶ ፡ ፈቃድህን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡንም ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ ያከናውንልህ ፡ ዘንድ ።
፴፩ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ተሰጥዎውን ፡ መልሱ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍጹም ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር ፡ የጌትነትህ ፡ ምሥጋና በሰማይና ፡ በምድር ፡ የመላ ፡ ነው ።
፴፪ ፤ ንፍቅ ፡ ቄስ ፡ ዕጣኑን ፡ ወገሮ ፡ ያቅርብለት ። እጁንም ፡ አጥኖ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ከሥጋውና ፡ ከደሙ ፡ ላይ ፡ ያሳርግ ።

ይ ፡ ካ ፡ እጆቹን ፡ ለሕማም ፡ ዘረጋ ፡ በርሱ ፡ ያመኑ ፡ ሕሙማንን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ታመመ ።

፴፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ መንግሥትከ ። ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ ሊቅ ፡ በውተ ፡ መንግሥትከ ። ተዘከረነ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ። በከመ ፡ ተዘከርኮ ፡ ለፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ እንዘ ፡ ሀሎከ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ቅዱስ ።

፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ዘተውህበ ፡ በፈቃዱ ፡ ለሕማም ሐመ ፡ ከመ ፡ ሕሙማነ ፡ ያድኅን ፡ ወያጽንዖ ሙ ፡ ለእለ ፡ ተንተኑ ። ግዱፋነ ፡ ይርከብ ፡ ወ ሙታነ ፡ ያሕዩ ፡ ወሞተ ፡ ይሥዐር ፡ ወማእ ሠረ ፡ ሰይጣን ፡ ይብትክ ።

፴፭ ፤ ፈቃደ ፡ አቡሁ ፡ ይፈጽም ፡ ወይኪድ ሲኦለ ፡ ወያርኁ ፡ አናቅጸ ፡ ሕይወት ።

፴፮ ፤ ለጻድቃን ፡ ያብርሆ ፤ ሥርዓተ ፡ ይትክ ል ፤ ጽልመተ ፡ ያእትት ፤ ወሕፃናተ ፡ ያልህቅ ወትንሣኤሁ ፡ ያግህድ ። በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ አመ ፡ ያገብእዎ ።

፴፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ አንሥኡ ፡ አደዊክሙ ፡ ቀሳውስት
፴፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ነሥአ ፡ ኅብስተ ፡ በእደዊሁ ፡ ቅዱሳት ፡ ወብፁዓት ፡ እለ ፡ እንበለ ፡ ነውር ።
በዝየ ፡ ያንሥእ ፡ ኅብስተ ።

፴፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ው እቱ ፡ በአማን ፡ ነአምን ።
፵ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አእኰተ ፡ ባረከ ፡ ወፈተተ ።
ቡራኬ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ ፡ በዝየ ፡ ያንቅዎ ።

ወመጠወ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ነጊሮ ፡ እንዘ ፡ ይብል ንሥኡ ፡ ብልዑ ፡ ዝ ፡ እማሬ ፡ ኅብስት ፡ ሥጋየ ውእቱ ፡ ለዘበእንቲአክሙ ፡ ይትፌተት ፡ ለ ኅድገተ ፡ ኃጢአት ።

፵፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ ነ አምን ፡ ወንትአመን ፡ ንሴብሐከ ፡ አ እግዚእነ ወአምላክነ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ነአምን ።

፵፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ሰበ ፡ ዘንተ ፡ ትገብሩ ፡ ተዝ

፴፫ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በመንግሥትህ ፡ አ ስበን ። አቤቱ ፡ ሊቅ ፡ ሆይ ፡ በመንግሥትህ ፡ አስበን ። አቤቱ ፡ በጌትነትህ ፡ አስበን ። ቅ ዱስ ፡ በሚሆን ፡ በዕፀ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ሳለ ህ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማንን ፡ እንዳሰብከው ።

፴፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ በፈቃዱ ፡ ለሕማም ፡ ተሰጠ ሕሙማንን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ታመመ ፤ የተፍ ገመገሙትንም ፡ ያጸናቸው ፡ ዘንድ ። የተጣሉ ትን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፤ የሞቱትንም ፡ ያድን ፡ ዘ ንድ ፡ ሞትንም ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ የሰይጣንን ም ፡ ማሠሪያ ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ።
፴፭ ፤ ያባቱን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ሲኦልንም ፡ ይረግጥ ፤ የሕይወትንም ፡ ደጅ ፡ ይከፍት ፡ ዘንድ ።
፴፮ ፤ ለጻድቃን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፤ ሥርዓት ንም ፡ ይተክል ፡ ዘንድ ፤ ጨለማን ፡ ያርቅ ፡ ዘ ንድ ፡ ሕፃናትንም ፡ ያሳድግ ፡ ዘንድ ፡ ትንሣኤ ውንም ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ። እርሱን ፡ አሳል ፈው ፡ በሰጡበት ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ።

፴፯ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ቀሳውስት ፡ እጆቻችሁን ፡ አንሡ
፴፰ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ነውር ፡ በሌለባቸው ፡ ቅዱሳን ብፁዓት ፡ በሚሆኑ ፡ እጆቹ ፡ ኅብስቱን ፡ አን ሥቶ ፡ ይዞ ።
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኅብስቱን ፡ ያንሣ ።
፴፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ እናምናለን ፡ ይህ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውነት ፡ እናምናለን ።
፵ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አመሰገነ ፤ ባረከ ፤ ቈረሰ ።
፫ት ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወጋ ፡ ወጋ ፡ ያድርገው ።

ይህ ፡ እማሬ ፡ ኅብስት ፡ ለኃጢአት ፡ ማስተሥ ረያ ፡ ስለናንተ ፡ የሚፈተት ፡ ሥጋዬ ፤ ነው ንሡ ፡ ብሉ ፡ ብሎ ፡ ነግሮ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙር ቱ ፡ ሰጣቸው ።

፵፩ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ እና ምናለን ፡ እንታመንማለንም ። ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እናመሰግንሃለን ። ይህ ፡ እርሱ ፡ እንደሆነ ፡ በውነት ፡ እናምናለን ።

፵፪ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ይህን ፡ በምታደርጉበት ፡

ከረ፡ ዚአየ፡ ግበሩ ። ወከማሁ፡ጽዋዐ፡ ወይን ቶሲሐክ፡ አእኰተክ፡ ባረክከ፡ ወቀዲሰከ፡ ወ ሀብከሙ ፤ ቡራኬ ፡ ፫ት ፡ ጊዜ ። በአማን ፡ ደምከ፡ ዝንቱ፡እማሬ ፡ ዘተክዐወ፡ በእንተ ፡ ኃጢአትነ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

ማ፫ ፤ ወይነብንቦ ፡ ለጽዋዕ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ በእደዉ ፡ ዘየማን ።

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ ነአምን ፡ ወንትአመን ።

ማ፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ይእዜኒ ፡ እግዚኦ ፡ እንዘ ፡ ን ዜከር ፡ ሞተከ ፡ ወትንሣኤከ ፡ ንትአመነከ ።

ማ፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ ንዜኑ ፡ ሞተከ ፡ እግዚኦ ፡ ወ ትንሣኤከ ፡ ቅድስተ ፡ ነአምን ፡ ዕርገተከ ፡ ወዳግመ ፡ ምጽአተከ ፤ ንሴብሐከ ፡ ወንትአ መነከ ፡ ንስእለከ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡ አ እግ ዚእነ ፡ ወምላክነ ።

ማ፮ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ወናቀርብ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ኅ ብስተ ፡ ወዘንተ ፡ ጽዋዐ ፡ እንዘ ፡ ነአኵተከ ፡ ለከ ፡ ለዘበሕቲትከ ፡ ዘእምዓለም ፡ መድኅን ፡ አምላክ ። እስመ ፡ አዘዝከነ ፡ ንቁም ፡ ቅድሜከ ፡ ወለከ ፡ ንትከሀን ።
በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንሕነ ፡ አግብርቲከ ፡ ንሴብ ሐከ ፡ እግዚኦ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

ማ፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ንስእለከ ፡ እግዚኦ ፡ ወናስ ተበቍዐከ ፡ ከመ ፡ ትፈኑ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወኃይለ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ እማሬ ፡ ኅብስት ፡ ወላ ዕለ ፡ ዝ ፡ እማሬ ፡ ጽዋዕ ።

ማ፰ ፤ ይረስዮ ፡ ሥጋሁ ፡ ቡራኬ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ። ወደሞ ፡ ቡራኬ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ። ዓዲ ፡ ላዕለ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ። ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።
እግዚኦ ፡ መሐረነ ፡ እግዚኦ ፡ መሐከነ ፡ እግ ዚኦ ፡ ተሣሃለነ ።

ማ፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ዓዲ ፡ ናቀርብ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ አኰቴተ ፡ ዘለዓለም ፡ ሥላሴ ፡ እግዚኦ ፡ አበ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወነ

ጊዜ ፡ የኔን ፡ መታሰቢያ ፡ አድርጉ ። እንደዚሁ ም ፡ የወይኑን ፡ ጽዋ ፡ ጨምረህ ፡ አመስግ ነህ ፡ ባርከህ ፡ አክብረህ ፡ ሰጠሃቸው ። ቡራኬ ፡ ፫ት ፡ ጊዜ ። ስለ ፡ ኃጢአት ፡ በውነት ፡ የ ፈሰሰ ፡ ይህ ፡ እማሬ ፡ ደምህ ፡ ነው ።
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።
ማ፫ ፤ ጽዋውን ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ይወዝውዘው

ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ እናምና ለን ፡ እንታመናለንም ፡
ማ፬ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አቤቱ ፡ አሁንም ፡ ሞትህንና ትንሣኤህን ፡ እያሰብን ፡ እናምንሃለን።
ማ፭ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ ሞትህንና ፡ ቅድ ስት ፡ ትንሣኤህን ፡ እንነግራለን ፤ ዕርገትህንና ዳግመኛም ፡ መምጣትህን ፡ እናምናለን ። እና መሰግንሃለን ፡ እናምንሃለንም ፡ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ እንለምንሃለን ፤ እንማል ድሃለንም ።

ማ፮ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ከዓለም ፡ መድኅን ፡ አምላክ ፡ የሆንህ ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ እያመሰገንህ ፤ ይህን ኅብስትና ፡ ይህን ፡ ጽዋ ፡ እናቀርብልሃለን ። በፊትህ ፡ ቆመን ፡ አንተን ፡ እናገለግል ፡ ዘን ድ ፡ አዘኸናልና ። ስለዚህ ፡ እኛ ፡ ባሮችህ ፡ አቤቱ ፡ እናመሰግንሃለን ።
ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ፡

ማ፯ ፤ ይ ፡ ካ ፡ አቤቱ ፡ በዚህ ፡ እማሬ ፡ ኅብስ ትና ፡ በዚህ ፡ እማሬ ፡ ጽዋ ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅ ዱስን ፡ ኃይልንም ፡ ትልክ ፡ ዘንድ ፡ እንለም ንሃለን ፡ እንማልድሃለን ።

ማ፰ ፤ የጌታችንና ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋውን ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፤ ደሙንም ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ለዘላለሙ ። ዳግመኛ ፡ በሁለቱ ፡ ላይ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ይባርክ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ፡ አቤቱ ፡ ማረን ፡ አቤቱ ፡ ራ ራልን ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ማ፱ ፤ ይ ፡ ካ ፡ ዳግመኛ ፡ ዘለዓለም ፡ ሦስት ለምትሆን ፡ ለአንተ ፡ ይህነን ፡ ምስጋና ፡ እና ቀርብልሃለን ። የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ አባት

ነፍስ፡ትርዕ ፡ወይሠወጥበ፡ቲ፡ለከ፡ዝ
ንቱ፡አምኃ ።

፶ ፤ አኮ፡መብልዐ፡ወመስቴ፡ዘአቅረብነ
ለቅድሳቲከ፡ግበር፡ለነ፡ኢይኩነነ፡ለኰነኔ
ወኢለዘርክየ፡ጸላዒ፡ወኢለኀጕል ። አላ፡
ፈውሰ፡ለሥጋነ፡ወለጽንዐ፡መንፈስነ ።

፶፩ ፤ እወ፡እግዚኦ፡አምላክነ፡ሀበነ፡በ
እንተ፡ስምከ፡ዐቢይ፡ንኵየይ፡እምኵሉ፡
ሕሊና፡ዘኢያሠምረከ ።
፶፪፤ እግዚኦ፡ ሀበነ፡ ይሰደድ፡እምኔነ፡
ኵሉ፡ምክረ፡ሞት፡ለዘበስምከ፡ተጽሕፈ፡
በውሳጢተ፡መንጦላዕት፡ በመቅደስከ፡ዘአ
ርያም ።

፶፫፤ ስመ፡ዚአከ፡ይሰማዕ፡ሞት፡ወይደ
ንግፅ፤ወቀላያት፡ይሰጠቃ፡ወጸላዒ፡ይት
ከየድ ።
መንፈስ፡ኀጕል፡ይርዐድ፡ወከይሲ፡ ይትገ
ኃሥ፡ወኢአሚን፡ ይርሐቅ፤ወዐላዊ፡ይት
መነደብ። መዓት፡ይኅሣዕ፡ ቅንዓት፡ኢይ
ብቋዕ፡ዝሉፍ፡ለይትገሠጽ ።
ወይሠረዉ፡መፍቀርያነ፡ወርቅ፡ፃማ፡ለይ
ሰስል ። ሐበሊ፡ ለይትነፃሕ፡ ወይዘርዘር፡
ኵሉ፡ዘፍጥረታት፡ኅምዝ ።
፶፬፤ ሀብ፡እግዚኦ፡ ለአዕይንተ፡ ልብነ፡
ውሳጥያት፡ከመ፡ኪያከ፡ይርአያ፡ ወይሰብ
ሓከ፡ወይወድሳከ፡እንዘ፡ ይዜክራከ፡ወይ
ትቀነያ፡ለከ፡እስመ፡አንተ፡በሕቴትከ፡መ
ከፈልቶን ።

፶፭፤ ወልዱ፡ ወቃሉ፡ ለእግዚአብሔር፡
ዘኵሉ፡ለከ፡ይትቀነይ፡ ለእለ፡ጸጋ፡ከሠ
ትከ፡ፈጽም፡ ወአጽንዕ ። ወእለ፡ በጸጋ፡
ፈውስ፡ዕቀብ ።
ለእለ፡በኀይለ፡ልሳን፡ ይሴብሑ፡አሚነ፡
ዘበቃለ፡ልሳን፡ተምሀሩ፡አርትዕ ።
እለ፡ይገብሩ፡ፈቃደከ፡ለዝሉፉ፡አድኅን፤
መዓስበ፡ሐውፅ፤ እጓለ፡ማውታ፡ተወከፍ
እለ፡በሃይማኖት፡አዕረፉ፡ተወከፍ ።

አቤቱ፡ፍጥረት፡ሁሉ፡ነፍስም፡የምትንቀ
ጠቀጥልህና፡ፍርሃት፡አድሮባት፡የሚኖር፤
ይህ፡ምስጋና፡ለአንተ፡ይገባል ።
፶፤ ለቅድሳትህ፡መብልንና፡መጠጥን፡ያ
ቀረብን፡አይደለም፤ለመፈራረጃ፡ለጠላትም
መሰደቢያ፡ ለጥፋትም፡ እንዳይሆንብን፡አ
ድርግልን ። ለሥጋችን፡ ደኅንነት፡ ለነፍሳ
ችንም፡ጽንዕ፡ይሁንልን፡እንጂ ።
፶፩፤ አዎን፡አቤቱ፡አምላካችን፡ስለ፡ስ
ምህ፡አንተን፡ደስ፡ከማያሰኝ፡አሳብ፡እን
ለይ፡ዘንድ፡መለየቱን፡ስጠን ።
፶፪፤ በአርያም፡ባለች፡በመቅደስህ፡መጋ
ረጃ፡ውስጥ፡ በስምህ፡ ከተጻፍን፡ከእኛ፡
የሞት፡ምክር፡ሁሉ፡ይርቅ፡ ዘንድ፡መራ
ቁን፡ስጠን ።

፶፫፤ ያንተን፡ስም፡ሰምቶ፡ሞት፡ይደንግ
ጥ፤ቀላያትም፡ይሠንጠቁ፡ጠላትም፡ይረገጥ።
የጥፋት፡መንፈስም፡ይንቀጥቀጥ፤ከይሲም፡
ይወገድ፤ አለማመንም፡ይራቅ ። ወንጀለኛ
ይቸገር፡ቍጣ፡ጸጥ፡ይበል፤ ቅናት፡ጥቅም
አያግኝ፤ኃጢአትን፡የሚያዘወትር፡ይገሠጽ።
ወርቅን፡የሚወዱ፡ ይነቀሉ፤ ድካም፡ይወ
ገድ፤ ሐሰተኛ፡ይጣል፤ መርዝ፡ያላቸው፡
የፍጥረቶች፡ወገን፡ሁሉ፡ይበተን ።

፶፬፤ አቤቱ፡ለአዕይንተ፡ልቡናችን፡ውስ
ጣዊ፡ብርሃንን፡ስጥ፤ እያሰቡህና፡ ላንተ፡
እየተገዙ፡አንተን፡ለይተው፡ ያከብሩህና፡
ያመሰግኑህ፡ዘንድ፤ዕድላቸው፡አንተ፡ብቻ
ነህና ።

፶፭፤ ሁሉ፡የሚገዛልህ፡የእግዚአብሔር፡
ቃሉና፡ልጁ፡ሆይ፡የገለጽህላቸውን፡ጸጋ፡
ፈጽም፡አጽናም፡በደኅንነት፡ ጸጋ፡ ያሉት
ንም፡ጠብቅ ።
በአንደበት፡ኃይል፡ለሚያመሰግኑ፡በአንደ
በት፡ቃል፡የተናገሩትን፡ሃይማኖት፡አቅና።
ሁለጊዜ፡ፈቃድህን፡የሚሠሩትን፡አድን፤
ባል፡የሌላትን፡ጐብኝ፡እናት፡አባት፡የሌ
ለውን፡ተቀበል፤ በሃይማኖት፡ ያረፉትንም
ተቀበል ።

፶፯ ፤ ሀበነ ፡ ለነኒ ፡ ክፍለ ፡ እግዚኦ ፡ ምስለ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳኒከ ፤ ሀበነ ፡ ኃይለ ፡ ናሥምርከ ፡ በከመ ፡ እሙንቱ ፡ አሥመሩከ ።

፶፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በኵሉ ፡ ልብ ፡ ናስተበቍዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ኅብረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ይጸግወነ ።

፶፱ ፤ ይ ፡ ሕ ፡ በከመ ፡ ሀሎ ፡ ሀልወ ወይሄሉ ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

በዝየ ፡ ይኄትም ፡ ሥጋ ፡ በደም ፡ ጠሚዖ ፡ በአጽባዕቱ ።

፷ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሕዝበከ ፡ ረዓይ ፡ በርትዕ ፡ ወቅድሳት ፡ ሀበነ ፡ እግዚኦ ፡ ለኵልነ ፡ ድማሬ ፡ ለእለ ፡ ንትሜጦ ፡ እምቅድሳቲከ ፡ ንጽገብ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወኃይለ ፡ ወጽንዐ ፡ ሃይማኖት ፡ በጽድቅ ።

፷፩ ፤ ከመ ፡ ለዝሉፉ ፡ ኪያከ ፡ ናእኵት ፡ ወወልደከ ፡ ወፍቁረከ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

፷፪ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ሀበነ ፡ ንኅበር ፡ በዘዚአከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወፈውሰነ ፡ በዝንቱ ፡ ጽርስፎራ ፡ ከመ ፡ ብከ ፡ ንሕየው ፡ ዘለኵሉ ፡ ዓለም ወለዓለመ ፡ ዓለም ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፷፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ቡሩክ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወቡሩክ ፡ ዘይመጽእ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይትባረክ ፡ ስመ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ፡ ቡሩክ ፡ ለይኩን ።

ይ ፡ ሕ ፡ ከማሁ ።

፷፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ፈንዎ ፡ ለጰራቅሊጦስ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ።

ይ ፡ ሕ ፡ ፈኑ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌነ ።

፷፭ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ተንሥኡ ፡ ለጸሎት ።
ይ ፡ ሕ ፡ እግዚኦ ፡ ተሣሃለነ ።
ይ ፡ ካ ፡ ሰላም ፡ ለኵልክሙ ።
ይ ፡ ሕ ፡ ምስለ ፡ መንፈስከ ።

፷፮ ፤ ጸሎተ ፡ ፈትቶ ።

ይ ፡ ካ ፡ ወካዕበ ፡ ናስተበቍዖ ፡ ዘኵሎ ፡ ትእ

፶፯ ፤ አቤቱ ፡ ለእኛም ፡ ከቅዱሳንህ ፡ ሁሉ ጋራ ፡ ዕድልን ፡ ስጠን ፤ እነርሱ ፡ ደስ ፡ እንዳሰኙህ ፡ ደስ ፡ እናሰኝህ ፡ ዘንድ ፡ ኃይልን ፡ ስጠን ።

፶፰ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ አምላካችንን እግዚአብሔርን ፡ እንማልደው ። ያማረ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አንድነት ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፶፱ ፡ ይ ፡ ሕ ፡ በፊት ፡ እንደነበረ ፡ ለዘላለሙ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ጠምቆ ፡ በደሙ ፡ ሥጋውን ፡ ይቀባ ።

፷ ፡ ይ ፡ ካ ፡ በቅንነትና ፡ በንጽሕና ፡ ወገኖችህን ፡ ጠብቅ ። እንጸግብ ፡ ዘንድ ፡ ከሥጋህ ከደምህ ፡ ለምንቀበል ፡ ለሁላችንም ፡ አቤቱ አንድነትን ፡ ስጠን ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ኃይልንም ፡ በእውነት ፡ የሃይማኖትንም ፡ ጽናት ፡ ስጠን ።

፷፩ ፤ ሁልጊዜ ፡ አንተን ፡ እናመሰግን ፡ ዘንድ ፤ ልጅህንና ፡ ወዳጅህን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ።

፷፪ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የአንተ ፡ በሚሆን ፡ በመንፈስ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ መሆንን ፡ ስጠን ፤ በዚህም ፡ ጽርስፎራ (በሥጋው ፡ በደሙ) አድነን ። ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ በምትሆን ፡ በአንተ ፡ ለዘላለሙ ፡ ሕያዋን ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፷፫ ፤ ይ ፡ ካ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ምስጉን ፡ ነው ። በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚመጣውም ፡ ምስጉን ፡ ነው ። የጌትነቱም ፡ ስም ፡ ይመስገን ፡ ይሁን ፡ ይሁን ፡ የተመሰገነ ይሁን ።

ይ ፡ ሕ ፡ እንደርሱ ።

፷፬ ፡ ይ ፡ ካ ፡ የጽድቅ ፡ መንፈስ ፡ ጰራቅሊጦስን ፡ ላከው ።

ይ ፡ ሕ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ ላክልን ።

፷፭ ፤ ይ ፡ ዲ ፡ ለጸሎት ፡ ተነሡ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።
ይ ፡ ካ ፡ ለሁላችሁ ፡ ሰላም ፡ ይሁን ።
ይ ፡ ሕ ከመንፈስህ ፡ ጋራ ።

፷፮ ፤ የመፈተት ፡ ጸሎት ።

ይ ፡ ካ ፡ ዳግመኛም ፡ ሁሉን ፡ የምትይዝ ፡ የጌ

ኀዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለእግዚእ ፡ ወመ
ድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፻፳፩፤ አገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ፡ አምላኪየ ፡ ዘት
ነብር ፡ ዲበ ፡ኪሩቤል ፡ ወተዐርፍ፡ በልዑላን
ታሕታነ ፡ ተአምር ፡ እስመ ፡ ውስተ ፡ ብርሃ
ን ፡ ሀሎከ ።
፻፳፪፤ ኦ ፡ ዘታዐርፎ ፡ ለዓለም ፡ ምሥጢረ ፡
ኅቡእ ፡ በዲበ ፡ መስቀል ፡ ዘአንተ ፡ አርአይ
ከ ፡ ወመኑ ፡ መሐሪ ፡ ወቅዱስ ፡ ዘከማከ ።

፻፳፫፤ እንቲአከ ፡ ሥልጣነ ፡ ዘወሀብኮሙ ፡
ለሐዋርያቲከ ፡ እለ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለከ ፡ በየውሃ
ተ ፡ ልብ ፡ ወእለ ፡ ያቄርቡ ፡ ለከ ፡ መዓዛ ፡ ሠ
ናየ ። ወበእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡
ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ዘኵሎ ፡ ይእኅዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ።

፻፳፬፤ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ ይትቀደስ ፡
ስምከ ፡ ትምጻእ ፡ መንግሥትከ ፡ ወይኩን ፡
ፈቃድከ ፡ በከመ ፡ በሰማይ ፡ ከማሁ ፡ በምድር
ሲሳየነ ፡ ዘለለዕለትነ ፡ ሀበነ ፡ ዮም ፡ ኅድግ ፡
ለነ ፡ አበሳነ ፡ ወጌጋየነ ፡ ከመ ፡ ንሕነኒ ፡ ንኅ
ድግ ፡ ለዘአበሰ ፡ ለነ ፤ ኢታብአነ ፡ እግዚኦ ፡
ውስተ ፡ መንሱት ፡ አላ ፡ አድኅነነ ፡ ወባልሐነ
እምኵሉ ፡ እኩይ ፡ እስመ ፡ ዚአከ ፡ ይእቲ ፡
መንግሥት ፡ ኃይል ፡ ወስብሐት ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም ።
፻፳፭፤ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ዘ
ኵሎ ፡ ትእኅዝ ፡ ንስእለከ ፡ ወናስተበቍዐከ ፡
እንቲአከ ፡ ሥልጣነ ፡ ኢታርሕቅ ፡ እምኔነ ።
፻፳፮፤ በከመ ፡ ሥልጣን ፡ ዘወሀብኮሙ ፡ ለሐ
ዋርያት ፡ እለ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለከ ፡ በየውሃተ ፡
ልብ ፡ ወእለ ፡ ያቄርቡ ፡ ለከ ፡ መዓዛ ፡ ሠናየ ።
ወበእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡
ዓለም ፡ አሜን ።

፻፳፯፤ ይ ፡ ሕ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክቲሁ ፡ ለ
መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ይቀውሙ፡ ቅድሜሁ፡ ለመ
ድኃኔ ፡ ዓለም ።

ታችንና ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንማልዳ
ለን ።
፻፳፩፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ በኪሩቤል ፡ የምት
ኖር ፡ በልዑላንም ፡ የምታርፍ ፡ ለአንተ ፡ እገ
ዛለሁ ። ትሑታንን ፡ ታውቃለህ ፡ በብርሃን ፡
አለህና ።
፻፳፪፤ ዓለሙን ፡ የምታሳርፈው ፡ ሆይ፡ በመ
ስቀል ፡ ላይ ፡ የተሠወረ ፡ ምሥጢርን ፡ ያሳየህ
አንተ ፡ ነህ ። እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ይቅር ፡ ባይና
ቅዱስ ፡ ማነው ።
፻፳፫፤ በልቡና ፡ ቅንነት ፡ ለሚያገለግሉህ ፡
በጎ ፡ መዓዛንም ፡ ለሚያቀርቡልህ ፡ ለሐዋር
ያት ፡ ያንተን ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠሃቸው ። ስለ
ጌታችን ፡ ስለ ፡ አምላካችንና ፡ ስለ ፡ መድኃ
ኒታችን ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይኸው
ም ፡ ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነው ።

፻፳፬፤ ይ ፡ ዲ ፡ ጸልዩ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ በሰማይ ፡ የምትኖ
ር ፡ ስምህ ፡ ይቀደስ ፡ መንግሥትህ ፡ ትምጣ።
ፈቃድህ ፡ በሰማይ ፡ እንደሆነች ፡ እንዲሁ ፡
በምድር ፡ ትሁን ። የዕለት ፡ እንጀራችንን ፡
ስጠን ፡ ዛሬ ። በደላችንንም ፡ ይቅር ፡ በለን ፡
እኛ ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንደምንል ።
ወደፈተናም ፡ አታግባን ፡ ከክፉ ፡ አድነን ፡ እ
ንጂ ፡ መንግሥት ፡ ያንተ ፡ ናትና ፡ ኃይልም ፡
ምስጋናም ፡ ለዘለዓለሙ ።

፻፳፭፤ ይ ፡ ካ ፡ ሁሉን ፡ የምትይዝ ፡ አምላክ
ችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ እንለምንሃለን ፡
እንማልድሃለንም ፤ ያንተን ፡ ሥልጣን ፡ ከኛ፡
እንዳታርቅ ።
፻፳፮፤ አንተን ፡ በልቡና ፡ ቅንነት ፡ ለሚያገለ
ግሉህ ፤ በጎ ፡ መዓዛንም ፡ ለሚያቀርቡልህ ፡
ለሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ሰጠሃቸው ፡ ሥልጣን ።
ስለ ፡ ጌታችንና ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ስለ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘ
ላለሙ ፡ አሜን ።
፻፳፯፤ ይ ፡ ሕ ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ የመላእ
ክት ፡ ሠራዊት ፡ በመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡
ይቆማሉ ።

፸፫ ፡ ወይኬልልዎ ፡ ለመድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋሁ ፡ ወደሙ ፡ ለመድኀኔ ፡ ዓለም ።
፸፬ ፡ ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለመድኀኔ ዓለም ፡ በአሚን ፡ ዚአሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንገኒ ።

፸፭ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ አርኀዉ ፡ ኆኀተ መኳንንት ።
፸፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ እለ ፡ ትቀውሙ ፡ አትሕቱ ርእሰክሙ ።
፸፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ዘትነብር ፡ ዲበ ፡ ኪሩቤል ፡ ወሱራፌል ፡ ወት ኔጽር ፡ ዲበ ፡ ሕዝብከ ፡ ወርስትከ ፡ ባርክ ፡ አግ ብርቲከ ፡ ወአእማቲከ ፡ ወደቂቆሙ ።

፸፰ ፡ ወክፍሎ ፡ ለዘይነሥእ ፡ እምክብርት ማዕድከ ፡ በንጹሕ ፡ ሕሊና ፡ ለኅድገተ ፡ ኃጢ አት ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትድምርት ፡ ለመ ድኀኒተ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ለዘበሰማያት ፡ መን ግሥት ፡ ወርስት ፡ በሞገስ ፡ ወበፈቃድ ። በዕዱ ፡ ወልድከ ፡ ዘቦቱ ፡ ለከ ፡ ምስሌሁ ፡ ወም ስለ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ስብሐት ፡ ወእኂዝ ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።
ቦ ፡ ኀበ ፡ ፫፻ት ፡ ተዘክር ፡ ሥጋ ፡ በል ።

፸፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ስግዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሃት ።
ይ ፡ ሕ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ ፡ ንሰግድ ፡ ወንሴብሐከ ።
፹ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሓ ።

፹፩ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተመጠወ ።
ይ ፡ ካ ፡ ኀዳፌ ፡ ነፍስ ፡ ለጻድቃን ፡ መርሕ ወለቅዱሳን ፡ ምክሕ ።
ሀበነ ፡ እግዚኦ ፡ አዕይንተ ፡ አእምሮ ወትረ ከ ፡ ያከ ፡ ይርአያ ፡ ወአእዛንነኒ ፡ ቃለ ፡ ዘበሕቲ ትከ ፡ ይስምዓ ። እምከመ ፡ ጸግበት ፡ ነፍስነ እምጸጋከ ፡ ልበ ፡ ንጹሐ ፡ ፍጥር ፡ ለነ ፡ ከመ ዘልፈ ፡ ዕበየከ ፡ ንለቡ ፡ ለኄር ፡ ወለመፍቀሬ ሰብእ ።

፹፪ ፡ አምላክነ ፡ ሥመራ ፡ ለነፍስ ፡ ዚአነ

፸፫ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለምን ፡ ያመሰግኑታል ፡ የመድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ።
፸፬ ፡ ወደ ፡ መድኀኔ ፡ ዓለም ፡ ፊት ፡ እንቅ ረብ ፡ እርሱን ፡ በማመን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንገ ዛለን ።
፸፭ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ ንፍቅ ፡ መኳንንት ፡ ደጆ ችን ፡ ክፈቱ ።
፸፮ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ የቆማችሁ ፡ ሰዎች ፡ ራሳ ችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ።
፸፯ ፡ ይ ፡ ካ ፡ በሱራፌልና ፡ በኪሩቤል የምትቀመጥ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ! ሕዝብህንና ፡ ርስትህን ፡ የምትመለከት ወንዶቹንና ፡ ሴቶቹን ፡ ባሮችህን ፡ ልጆቻቸ ውንም ፡ ባርክ ።
፸፰ ፡ ኃጢአትን ፡ ለማስተሥረይ ፡ በንጹሕ ሕሊና ፡ ከክብርት ፡ ማዕድህ ፡ ለሚቀበል ፡ አድ ለው ፡ ለሥጋና ፡ ለነፍስ ፡ መድኀኒት ፡ ከመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ በልዕልና ያለ ፡ መንግሥትን ፡ ርስትንም ፡ ለመውረስ ፡ በባለሟልነትና ፡ በፈቃድ ። በአንድ ፡ በልጅህ በርሱ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ጽንዕ ፡ ለአንተ ፡ ይገባል ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ ዛሬ ም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።
እንዲ ፡ ለከ ፡ በሰው ፡ ጸሎት ፡ ፈትቶ ፡ ፈንታ ፡ የ፫ቱ ፡ ፫ትን ፡ ተዘክር ፡ ሥጋን ፡ በል ፡ (ቅዳ ፡ ሠረ ፡ ቁ ፡ ፺፰—፺፱ ፡ እይ)
፸፱ ፡ ይ ፡ ዲ ፡ በፍርሃት ፡ ሁላችሁ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ስገዱ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ፡ በፊትህ ፡ እንሰግዳለን ፡ እና መሰግንሃለንም ።
፹ ፡ ይ ፡ ካ ፡ ጸሎተ ፡ ንስሓ ። (ቅዳ ፡ ሐዋ ፡ ቁ ፡ ፸፱—፹፰ ፡)
፹፩ ፡ ከተቀበሉም ፡ በኋላ ። (ቅዳ ፡ ሐዋ ፡ ቁ ፡ ፹፱—፺፴)
ይ ፡ ካ ፡ ነፍስን ፡ የምታሰማር ፡ ለጻድቃን ፡ መሪ ለቅዱሳን ፡ መመኪያ ።
አቤቱ ፡ የዕውቀት ፡ ዓይኖችን ፡ ስጠን ። ዘወ ትር ፡ አንተን ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ጆሮቻችንም ፡ ያንተን ፡ ብቻ ፡ ቃል ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ። ሰው ነታችን ፡ ከጸጋህ ፡ ከጠገበች ፡ ዘንድ ፡ ንጹሕ ልቡናን ፡ ፍጠርልን ። ቸር ፡ ሰው ፡ ወዳጅ የምትሆን ፡ አቤቱ ፡ ገናንነትህን ፡ ዘወትር ፡ እና ውቅ ፡ ዘንድ ።
፹፪ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፡ ሰውነታችንን

ወሕሊና ፡ ንጹሐ ፡ ዘኢይጸንን ፡ ጸግወነ ፤ ዘተ
መጠነ ፡ ዚአከ ፡ ሥጋ ፡ ወእንቲአከ ፡ ደመ
ንሕነ ፡ አግብርቲከ ፡ ትሑታን ።
እስመ ፡ መንግሥት ፡ ዚአከ ፡ እግዚእ ፡ ቡሩክ
ወስቡሕ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ
ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።
፹፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ።
ባርክ ፡ አግብርቲከ ፡ ወአእማቲከ ፡ ክድን ፡ ወር
ዳኢ ፡ ወሠርዓ ፡ በኃይለ ፡ መላእክቲከ ፤ ዕቀብ
ወአጽንዕ ፡ ላዕለ ፡ ፈሪሆት ፡ ስምከ ፡ ቅዱስ ።
በዘዚአከ ፡ ዕበይ ፡ አሠርጉ ፡ ዘዚአከ ፡ የሐልዩ
ወዘዚአከ ፡ ይእመኑ ፡ ወዘዚአከ ፡ ይፍቅዱ ።

፹፬ ፤ ሱላሜ ፡ ዘእንበለ ፡ አበሳ ፡ ወመዓት
በኢጽርዓት ፡ ጸጉ ።
በ፩ዱ ፡ ወልድከ ፡ ዘቦቱ ፡ ለከ ፡ ምስሌሁ ፡ ወ
ምስለ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ስብሐት ፡ ወእኂዝ
ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።

ውዳዴት ፡ የማይዘነብል ፡ ንጹሕ ፡ ሕሊናንም
ስጠን ፤ ያንተን ፡ ሥጋና ፡ ያንተን ፡ ደም ፡ የተ
ቀበልን ፡ እኛ ፡ ባሮችህ ፡ ትሑታን ፡ ነን ።
አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያንተ ፡ መን
ግሥት ፡ አቤቱ ፡ ክቡር ፡ ምስጉንም ፡ ነውና ፡
ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ።
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።
፹፫ ፡ ይ ፡ ካ ፡ አንብሮ ፡ እድ ።
ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ባሮችህን ፡ ባርክ ፡
ሠውር ፤ አርዳም ። በመላእክትም ፡ ኃይል
አሰናብት ፤ ጠብቅ ፤ ቅዱስ ፡ የሚሆን ፡ ስም
ህንም ፡ በመፍራት ፡ አጽና ። ባንተ ፡ ገናን
ነት ፡ አስጊጻቸው ፤ ያንተን ፡ ነገር ፡ ያስቡ
ዘንድ ። ያንተንም ፡ ነገር ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡
ያንተንም ፡ ነገር ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ።
፹፬ ፤ ያለበደልና ፡ ያለ ፡ ቍጣ ፡ ሥራ ፡ ባለ
መፍታትና ፡ ባለማቋረጥ ፡ አንድነትን ፡ ስጥ ።
በአንድ ፡ ልጅህ ፡ በርሱ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ ፅንዕ
ለአንተ ፡ ይገባል ። ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመንፈስ
ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ ዛሬም ፡ ዘወትርም ፡ ለዘላለሙ ፡
ይ ፡ ሕ ፡ አሜን ።